Arlington Public Schools

# የተማሪ ምዝገባ የማረጋገጫ ዝርዝር

**በአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ ሰነዶች፦**

1. **የልጁ እድሜና ህጋዊ ስም ማረጋገጫ**

☐ **ኦሪጂናል የልደት የምስክር ወረቀት -** ዋናው የልደት የምስክር ወረቀት በእንግሊዝኛ ካልሆነ፣ ይፋዊ ትርጉም ያስፈልጋል።

2. **የነዋሪነት ማረጋገጫ**

ወላጆች ወይም በፍርድ ቤት ሃላፊነት የተሰጣቸው ህጋዊ አሳዳጊዎች ከልጃቸው ጋር በአርሊንግተን ካውንቲ እንደሚኖሩ ማረጋገጫ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

**<u>የቤት ባለቤት ለሆኑ እና ተከራይ ለሆኑ ቤተሰቦች</u>**

ወላጆቹ ወይም በፍርድ ቤት ሃላፊነት የተሰጣቸው ህጋዊ አሳዳጊዎቹ በባለቤትነት በያዙት ወይም በተከራዩት ቤት ውስጥ ልጁ የሚኖር ከሆነ፣ **ሶስት (3) ሰነዶች መቅረብ አለበት።**

**ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ አንዱ (1) መቅረብ አለበት፦**

☐ **ስመርስት -** የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውንና በአርሊንግተን እንደሚኖሩ የሚያሳይ፣

☐ **የአሁኑ የሊዝ ውል -** በወላጆች/አሳዳጊ ስም በአከራይና ተከራይ ወይም በተከራይና ባለንብረት የተፈረመ መሆኑን የሚያሳይ፣

☐ **የቤት ግዢ ሰነድ -** ስመርስቱ ካልተመዘገበ እና ከአዲስ የቤት ግዢ የተገኘ ሰነድ፣

**እና**

**የወላጆቹ/ህጋዊ አሳዳጊዎቹ ስምና አድራሻ የሚያሳዩ ከሚከተሉት ሁለት (2) ደጋፊ ሰነዶች መቅረብ ይኖርባቸዋል።**

የአሁኑ የፌዴራል፣ የስቴት ወይም የንብረት ግብር ተመላሾች፣ የአሁን የደመወዝ ክፍያ ገላጭ፣ የአሁኑ የተሽከርካሪ ምዝገባ ካርድ፣ የአሁን የፍጆታ ክፍያዎች፣ የአሁኑ አድራሻ ያለው የሚያገለግል የቨርጂኒያ መንጃ ፍቃድ ወይም በመንግስት የተሰጠ መታወቂያ፣ከአርሊንግተን ካውንቲ የገንዘብ ድጋፍ ሰነድ፣ የአሁኑ የባንክ መግለጫ፣ በአድራሻቸው የተመዘገበ ወቅታዊ የቤት ባለቤትነት ወይም የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ፣ የመራጮች የምዝገባ ካርድ፣ የአሁኑ የገቢ ግብር ቅጽ 1099 ወይም ተቀናሽ W2

**<u>በጋራ መኖሪያ ቤት (የሌላ ሰው መኖሪያ ቤት) ለሚኖሩ ቤተሰቦች</u>**

ወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች በሌላ ሰው መኖርያ ቤት ከልጃቸው ጋር በጋራ የሚኖሩ ከሆኑ፣ **አምስት (5) ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፡፡**

**የሚከተሉት ሶስት (3) ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፦**

☐ **ቅጽ A-** የወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ/የአዋቂ ተማሪ የነዋሪነት ማረጋገጫ ጽሑፍ፣

☐ **ቅጽ B-** የአርሊንግተን ነዋሪ ማረጋገጫ መግለጫ ጽሑፍ፣

☐ **ስመርስት ወይም የአሁኑ የሊዝ ስምምነት ወይም የቤት ግዢ ሰነድ** (ስመርስቱ ካልተመዘገበ እና ከአዲስ የቤት ግዢ የተገኘ ሰነድ)

**እና**

**የወላጆቹ/ህጋዊ አሳዳጊዎቹ ስምና አድራሻ የሚያሳዩ ከሚከተሉት ሁለት (2) ደጋፊ ሰነዶች መቅረብ ይኖርባቸዋል።**

የአሁኑ የፌዴራል፣ የስቴት ወይም የንብረት ግብር ተመላሾች፣ የአሁን የደመወዝ ክፍያ ተመላሽ፣ የአሁኑ የተሽከርካሪ ምዝገባ ካርድ፣ የአሁን የፍጆታ ክፍያዎች፣ የአሁኑ አድራሻ ያለው የሚያገለግል የቨርጂኒያ መንጃ ፍቃድ ወይም በመንግስት የተሰጠ መታወቂያ፣ከአርሊንግተን ካውንቲ የገንዘብ ድጋፍ ሰነድ፣ የአሁኑ የባንክ መግለጫ፣ በአድራሻቸው የተመዘገበ ወቅታዊ የቤት ባለቤትነት ወይም የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ፣ የመራጮች የምዝገባ ካርድ፣ የአሁኑ የገቢ ግብር ቅጽ 1099 ወይም ተቀናሽ W2

የመኖሪያ ቅጾች A እና B በዚህ የAPS ድህረገጽ https://www.apsva.us/registration/required-documents/ ላይ ይገኛሉ፡፡

3. **የወላጅ ማንነት እና ከተማሪው ጋር ያላቸው ግንኙነት ማረጋገጫ ፡-**

ወላጆች ወይም በፍርድ ቤት ሃላፊነት የተሰጣቸው ህጋዊ አሳዳጊዎች ትክክለኛ ፎቶ ያለበት ከመንግስት የተሰጠ መታወቂያ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከሚከተሉት ውስጥ <u>አንዱ (1)</u> መቅረብ አለበት፦

☐ ማንኛውም ከመንግስት የተሰጠ ፎቶ ያለበት መታወቂያ ☐ የመንጃ ፈቃድ ☐ ፓስፖርት

**በአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ ቅጾች**

☐ **የተማሪ መመዝገቢያ ቅጽ -** አዲስ ወይም በድጋሚ ለሚመዘገቡ ከቅድመ መዋእለ ሕጻናት-12ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ ይህንን ቅጽ ይሙሉ፡፡

☐ **የቅድመ መዋእለ ሕጻናት ተሞክሮ -** ለመዋእለ ሕጻናት ለሚመዘገቡ ተማሪዎች ይህንን ቅጽ ይሙሉ፡፡

**የሕክምና ሰነዶች**

ለምዝገባ ግዴታ የሚያስፈልግ ባይሆንም፣ ልጁ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የሚከተሉትን ለት/ቤቱ መቅረብ አለባቸው።

የክትባት መዝገቦች (የቅድመ መዋእለ ሕጻናት - 12ኛ ክፍል)፣ የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ ወይም ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ባሉት 12 ወራት ውስጥ የተደረገ ምርመራ (ቅድመ መዋእለ ሕጻናት - 12ኛ ክፍል) እና ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ባሉት 12 ወራት ውስጥ የተደረገ አካላዊ ምርመራ (ቅድመ መዋእለ ሕጻናት - 5ኛ ክፍል )፡፡

**ትምህርታዊ ሰነዶች**

ለምዝገባ ግዴታ የሚያስፈልግ ባይሆንም፣ እባክዎን የትምህርት ቤት ትምህርታዊ መዝገቦችን ካለዎት ወይም ከቀድሞው ትምህርት ቤት የወጡ ይፋዊ የትምህርት ማስረጃዎችን ያቅርቡ፡፡

የሚመለከትዎት ከሆነ፣ የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም (IEP)፣ የ504 እቅድ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ወይም ተሰጥኦ ያላቸው መዝገቦችንም ያቅርቡ፡፡

ሁሉም የመመዝገቢያ ቅጾች በAPS ድረገጽ https://www.apsva.us/registration/ ላይ ይገኛሉ።